

# የዑዙዋው ጀግና

## ከሕብስቱ ያዕብዮ ፤ ኖርዌይ

የብዙሃኑ ጠበቃ የሞናርኪው የጎን ውጋት
የተማሪው አደራጅ የትግል ታክቲክ ቋት
የ66ቱ ተዋናይ ጀግናው አይበገሬ
እድሜውን የፈጀው ብሎ እንቢኝ ለአገሬ
ወርቅን በሳት እንዲሉ
በትግል የተፈተነው ባለድሉ
የመከራን ቂጣ እየጠፈጠፈ
ሕይወቱን በሙሉ ለሕዝብ ጥቅም ያሳለፈ
ሃቅ አስዋጪው አስተማሪው ደብተራ
የማይሸጥ ጭንቅላት ለተማሪው ያፈራ
እንዲያም ሲል በትግሉ ሜዳ
በጠላቶቹ ዱላ ብዛት በጥኑ የተጎዳ
እርሱ ለቃኘው ቅኝት ባዕድ ሆኖ
በሦስት መንግሥት ሹምባሾች ተኮንኖ
አለሁ ይላል አልሞት ብሎ
በመቀሌው ጉድጓድ ተጥሎ!